# የሲ.አር.ቢ.ቲ አገልግሎት የተጠቃሚዎች መመሪያ

ጥሪ በሚያደርጉበት ጊዜ የተለመደ የደወል ድምጽ መስማት ተሰላችተዋል? ወዳጅ ዘመዶችዎ ሲደውሉ አዝናኝ ሙዚቃ እና ዜማ ማስደመጥ ይፈልጋሉ? ወይም ፍቅረኛዎ ሲደውሉልዎ የመረጡትን አስደሳች ዜማ ማስደመጥ ይፈልጋሉ? እንግዲያውስ የሲ.አር.ቢ.ቲ አገልግሎት ይህን ህልምዎን እውን ያደርግልዎታል፡፡ የኢትዮ ቴሌኮም የሲ.አር.ቢ.ቲ አገልግሎትን አሁኑኑ ይቀላቀሉ፡፡

# የሲ.አር.ቢ.ቲ አገልግሎት ምንድን ነው?

የሲ.አር.ቢ.ቲ አገልግሎት የሞባይል ስልክ ተጠቃሚዎች ጥሪ በሚያደርጉበት ጊዜ ከተለመደው የደወል ጥሪ የተለየ ሙዚቃ እንዲያደምጡ የሚያስችል አገልግሎት ነው፡፡ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች እንደፍላጎታቸው አንድ ዘፈን ለሁሉም ደዋዮች ወይም በአድራሻ ማህደር ውስጥ ለሚገኙ የተለያዩ ደዋዮች የተለያዩ ዘፈኖችን በመመደብ እንዲደመጥ ማድረግ ይችላሉ፡፡

> ለምሳሌ፡- ደዋይ “ሀ” ወደ ”ለ” ጥሪ እያደረገ ቢሆን እና ጥሪ ተቀባዩ (ለ) የሲ.አር.ቢ.ቲ አገልግሎት ተጠቃሚ ከሆነ ደዋይ “ሀ” በጥሪ ተቀባይ (ለ) የተመደበለትን ሲ.አር.ቢ.ቲ ወይም ጥሪ ተቀባዩ (ለ) ለሁሉም ደዋዮቹ እንዲደመጥ ያደረገውን ሲ.አር.ቢ.ቲ ያደምጣሉ፡፡

| ክንውን | መግለጫ |
|---|---|
| **የአገልግሎቱ ደንበኛ ለመሆን** | በአጭር የጽሑፍ መልዕክት ወደ 822 **A ብለው መላክ**<br>በድረ ገጽ፡ 1. ወደ ሲ.አር.ቢ.ቲ ድረ ገጽ www.crbt.et በመሄድ መግቢያን መጫን<br>2. የስልክ ቁጥርዎን በማስገባት የማረጋገጫ ኮድ ማግኛውን መጫን<br>3. የተላከልዎትን የማረጋገጫ ኮድ በማስገባት መደበኛ ሲ.አር.ቢ.ቲ የሚለውን መምረጥ<br>4. በመጨረሻም መግቢያውን መጫን |
| **አዲስ ሲ.አር.ቢ.ቲ ለመግዛት** | አጭር የጽሑፍ መልዕክትን በመጠቀም:<br>1. ከሲ.አር.ቢ.ቲ ድረ ገጽ www.crbt.et የሚፈልጉትን ሲ.አር.ቢ.ቲ ይምረጡ<br>2. ከመረጡት ሲ.አር.ቢ.ቲ ጎን የሚገኘውን የሲ.አር.ቢ.ቲውን ኮድ ይውሰዱ<br>3. የሲ.አር.ቢ.ቲውን ኮድ ወደ 822 በአጭር የጽሑፍ መልዕክት ይላኩ፤ |

| | |
|---|---|
| ስለ አገልግሎት ክፍያ | የደንበኝነት ክፍያ፡ በነጻ<br>ወርሃዊ ኪራይ፡ 5ብር ተ.እ.ታን ጨምሮ<br>የሲ.አር.ቢ.ቲ ክፍያ፡ ለሀገር ውስጥ ሲ.አር.ቢ.ቲ 5 ብር ተ.እ.ታን ጨምሮ እና ለዓለም አቀፍ ሲ.አር.ቢ.ቲ 7 ብር ተ.እ.ታን ጨምሮ<br>ወደ 822 የሚደረግ አጭር የጽሁፍ መልዕክት በነጻ |
| አገልግሎቱን እንዳይሰራ ለማድረግ | ወደ 822 በአጭር የጽሑፍ መልዕክት DAC ብለው ይላኩ |
| አገልግሎቱን እንዲሰራ ለማድረግ | ወደ 822 በአጭር የጽሑፍ መልዕክት AC ብለው ይላኩ |
| ለሌላ ሰው የሲ.አር.ቢ.ቲ ስጦታ ለማበርከት | በአጭር የጽሑፍ መልዕክት G የሚያበረክቱት ሲ.አር.ቢ.ቲ ኮድ እና ስጦታ የሚያበረክቱለት ሰው ስልክ ጽፈው ወደ 822 ይላኩ፡፡ |
| ደንበኝነትዎን ለማቋረጥ | በአጭር የጽሑፍ መልዕክት ወደ 822 U ብለው ይላኩ |
| ድጋፍ ቢያስፈልግዎ | ድጋፍ ለማግኘት በአጭር የጽሑፍ መልዕክት ወደ 822 H ብለው ይላኩ ወይም የኢትዮ የሲ.አር.ቢ.ቲ ድረ ገጽ www.crbt.et ን ይጎብኙ፡፡ |



## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ጥ. የአገልግሎቱ ደንበኛ ለመሆን የተለየ የስልክ ቀፎ ያስፈልገኛል?**

**መ. አያስፈልግዎትም፤ አገልግሎቱ በሁሉም አይነት የስልክ ቀፎዎች የሚሰራ በመሆኑ የተለየ የስልክ ቀፎ አያስፈልግዎትም**

**ጥ. እንዴት ነው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለመሆን መመዝገብ የምችለው?**

**መ.ለአገልግሎቱ ለመመዝገብ በአጭር የጽሑፍ መልዕክት 822 ላይ A ብለው ይላኩ ወይም የሲ.አር.ቢ.ቲን ድረ ገጽ** www.crbt.et **ን ይጎብኙ፣**

**ጥ. መመዝገቤን እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ?**

**መ. በአጭር የጽሑፍ መልዕክት ወይም ድረ ገጽን በመጠቀም ከተመዘገቡ በኋላ የደንበኝነት ጥያቄዎን ክንውን ውጤት የሚያረጋግጥ አጭር የጽሑፍ መልዕክት ይደርስዎታል፡፡**

**ጥ. በመመዝገቤ የማገኘው ነገር ምንድን ነው?**

**መ. የተሳካ የደንበኝነት ምዝገባ የሚያደርጉ ሁሉም ደንበኞች ነጻ ሲ.አር.ቢ.ቲ ያገኛሉ፡፡**

**ጥ. በምዝገባ ወቅት ከሚሰጠኝ መደበኛ ሲ.አር.ቢ.ቲ የተለየ የራሴን ተመራጭ ዘፈን መምረጥ እችላለሁ?**

መ. አዎን፣ የሚፈልጉትን ዘፈን በመምረጥ የሲ.አር.ቢ.ቲ ምርጫዎ ማድረግ ይችላሉ፣ አገልግሎት ላይ ከሚገኙ ሁሉም ሲ.አር.ቢ.ቲዎች መካከል ለመምረጥ የሲ.አር.ቢ.ቲ ድረ ገጽን www.crbt.et ይጎብኙ፤ በተጨማሪም ካሉት ሲ.አር.ቢ.ቲዎች ውስጥ ምርጥ አስሩን ለማግኘት ወደ 822 በአጭር የጽሑፍ መልዕክት TOP ብለው ይላኩ፤

**ጥ. የመረጥኩትን ሲ.አር.ቢ.ቲ አጭር የጽሁፍ መልዕክትን በመጠቀም እንዴት መግዛት እችላለሁ?**

መ. የመረጡትን ሲ.አር.ቢ.ቲ  ኮድ ወደ 822 በአጭር የጽሑፍ መልዕክት በመላክ መግዛት ይችላሉ፡፡ ድረገጽን በመጠቀም ለመግዛት ድረ ገጽ ላይ የተገለጹ ሂደቶችን ይከተሉ፡፡

**ጥ. የገዛኋቸውን ሲ.አር.ቢ.ቲዎች የማስቀምጥበት የግል ማህደር ይኖረኛልን?**

መ. አዎን፣ የገዟቸውን ሲ.አር.ቢ.ቲዎች አስቀምጠው እየለዋወጡ መጠቀም እንዲችሉ እስከ አምስት ሲ.አር.ቢ.ቲዎችን መያዝ የሚችል የግል ማህደር ይኖርዎታል፡፡

**ጥ. የግል ማህደሬ ውስጥ የሚገኙ ሲ.አር.ቢ.ቲዎችን እንዴት ማየት እችላለሁ?**

መ. ወደ 822 በአጭር የጽሑፍ መልዕክት P ብለው በመላክ  የግል ማህደርዎ ውስጥ የሚገኙ ሲ.አር.ቢ.ቲዎችን ማየት ይችላሉ፡፡ እንደዚሁም በድረ ገጽ www.crbt.et ላይ የእኔ ሲ.አር.ቢ.ቲዎች ገጽ የሚለው ውስጥ በመግባት የግል ማህደርዎ ውስጥ ያሉ ዝርዝሮችን ማየት ይችላሉ፡፡

**ጥ. የግል ማህደሬ ውስጥ ከሚገኙ ሲ.አር.ቢ.ቲዎች ውስጥ በመምረጥ እንዲደመጥ ማድረግ እንዴት እችላለሁ?**

መ. ወደ 822 በአጭር የጽሑፍ መልዕክት SN እና የመረጡትን ሲ.አር.ቢ.ቲ ኮድ በመላክ እንዲደመጥ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የሲ.አር.ቢ.ቲው ኮድ 132456 ቢሆን SN132456 ወደ 822 በመላክ ለደዋዮችዎ እንዲደመጥ ማድረግ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

**ጥ. የግል ማህደሬ ውስጥ የሚገኙ ሲ.አር.ቢ.ቲዎችን እንዴት ማጥፋት እችላለሁ?**

መ. የመረጡትን ሲ.አር.ቢ.ቲ  ከግል ማህደርዎ ውስጥ ለማጥፋት det እና ማጥፋት የፈለጉትን ሲ.አር.ቢ.ቲ ኮድ ወደ 822 በመላክ ማጥፋት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ማጥፋት የሚፈልጉት ሲ.አር.ቢ.ቲ ኮድ 132456 ቢሆን det132456 ወደ 822 በመላክ ከግል ማህደርዎ ውስጥ እንዲጠፋ ማድረግ ይችላሉ፡፡

**ጥ. ለአገልግሎቱ የምከፍለው ክፍያ ምን ያህል ነው?**

መ. ለአገልግሎቱ ደንበኝነት ለመመዝገብ ምንም ክፍያ አይጠየቁም፤ የሀገር ውስጥ ሲ.አር.ቢ.ቲ ለመግዛት የአንድ ጊዜ ክፍያ 5 ብር ይከፍላሉ፤ ለዓለም አቀፍ ሲ.አር.ቢ.ቲ ደግሞ የአንድ ጊዜ ክፍያ  7 ብር ይከፍላሉ፤ በተጨማሪም ደንበኞች በየወሩ 5 ብር የአገልግሎት ኪራይ ይጠየቃሉ፡፡ ወደ 822 የሚደረጉ ሁሉም የአጭር ጽሑፍ መልዕክቶች ክፍያ አይጠየቅባቸውም፡፡

**ጥ. የሲ.አር.ቢ.ቲ ተጠቃሚ ከሆንኩ በኋላ የምጠቀምበት ሲ.አር.ቢ.ቲ እያለኝ ሌላ አዲስ ሲ.አር.ቢ.ቲ ብገዛ ተጨማሪ ክፍያ እጠየቃለሁ?**

መ. አዎን፣ የግል ማህደርዎ እስከሚችለው የሲ.አር.ቢ.ቲ ብዛት(5 ሲ.አር.ቢ.ቲ) በሚገዙበት ወቅት ሁሉ ለእያንዳንዱ አዲስ የሀገር ውስጥ ሲ.አር.ቢ.ቲ 5ብር ለዓለም አቀፍ ሲ.አር.ቢ.ቲ ደግሞ 7 ብር ክፍያ ይጠየቃሉ፡፡

**ጥ. ለሌላ ሰው የሲ.አር.ቢ.ቲ ስጦታ ገዝቼ ማበርከት እችላለሁን?**

መ. አዎን፣ የሲ.አር.ቢ.ቲ ተጠቃሚ ደንበኛ ለሆነ ሌላ ሰው የሲ.አር.ቢ.ቲ ስጦታ ማበርከት ይችላሉ፤ ለሚያበረክቱት የሀገር ውስጥ ሲ.አር.ቢ.ቲ 5ብር ለዓለም አቀፍ ሲ.አር.ቢ.ቲ ደግሞ 7 ብር ክፍያ ይጠየቃሉ፤ ሲ.አር.ቢ.ቲ በስጦታ ለማበርከት

በአጭር የጽሑፍ መልዕክት G  የሚያበረክቱት ሲ.አር.ቢ.ቲ ኮድ እና ስጦታ የሚያበረክቱለት ሰው ስልክ ጽፈው ወደ 822 ይላኩ፡፡

ማስታወሻ፡ ስጦታውን በአጭር የጽሑፍ መልዕክት በሚልኩበት ጊዜ በሲ.አር.ቢ.ቲ ኮዱ እና ስጦታውን በሚልኩላቸው ሰው ስልክ ቁጥር መካከል የአንድ ፊደል ክፍተት መኖር አለበት፡፡

ለምሳሌ፡ የሲ.አር.ቢ.ቲው ኮድ 123529 እና የሚያበረክቱላቸው ሰው ስልክ ቁጥር 0911000000 ቢሆን ስጦታውን የሚልኩት እንደሚከተለው ነው፡፡ G123529 0911000000 ጽፈው ወደ 822 ይልካሉ፡፡

**ጥ. ፈጣን የሲ.አር.ቢ.ቲ ግዢ አገልግሎት ማለት ምን ማለት ነው?**

መ. ፈጣን የሲ.አር.ቢ.ቲ ግዢ ማለት ስልክ በሚደውሉበት ወቅት የደወሉላቸው ደንበኛ የሚጠቀሙበትን ሲ.አር.ቢ.ቲ ቢወዱት ወዲያውኑ የራስዎ ማድረግ እንዲችሉ የሚያግዝ አገልግሎት ነው፤ ፈጣን የሲ.አር.ቢ.ቲ ግዢ በመጠቀም እያዳመጡ ያሉትን ሲ.አር.ቢ.ቲ የራስዎ ለማድረግ ሲ.አር.ቢ.ቲውን እያዳመጡ እያሉ ስልክዎ ላይ የኮከብ ምልክትን (*) በመጫን ጥሪውን ማቋረጥ ይኖርብዎታል፣ ከዚያም ሲ.አር.ቢ.ቲውን ለመግዛት በቂ ሂሳብ ካለዎት ወዲያውኑ የግል ማህደርዎ ውስጥ ያገኙታል፡፡

**ጥ. የሚደውሉልኝ ደንበኞች የተለያዩ ሲ.አር.ቢ.ቲዎችን እንዲያደምጡ ማድረግ እችላለሁ?**

መ. አዎን፣ የኢትዮ ሲ.አር.ቢ.ቲ ድረ ገጽ www.crbt.et ላይ በመሄድ በአድራሻ ማህደርዎ ውስጥ ለሚገኙ የተለያዩ ደዋዮች የተለያዩ ሲ.አር.ቢ.ቲዎች መመደብ ይችላሉ፡፡

**ጥ. በተለያዩ ጊዜያት የሚደመጡ የተለያዩ ሲ.አር.ቢ.ቲዎችን በመምረጥ እንዲደመጡ ማድረግ እችላለሁ**

መ. አዎን ይችላሉ፣ የኢትዮ ሲ.አር.ቢ.ቲ ድረ ገጽ www.crbt.et ላይ በመሄድ በተለያየ ጊዜ የሚደመጡ የተለያዩ ሲ.አር.ቢ.ቲዎችን መምረጥ ይችላሉ፤ ለምሳሌ ጠዋት ጠዋት የሚደመጥ፣ በበዓላት ቀን የሚደመጥ፣ በፍቅረኛሞች ቀን የሚደመጥ ... ወዘተ በማለት መምረጥ ይችላሉ፡፡

**ጥ. ወርሃዊ ኪራዩ ተግባራዊ የሚሆነው እንዴት ነው?**

መ. ወርሃዊ ኪራዩ ተግባራዊ የሚሆነው ደንበኛው ሲ.አር.ቢ.ቲውን መጠቀም ከጀመሩበት ቀን ጀምሮ በሚኖሩት 30 ቀናት እንደ አንድ ወር እየተቆጠሩ ደንበኞች ክፍያ ይጠየቃሉ፡፡

**ጥ. ለወርሃዊ ኪራይ የሚከፈል በቂ ሂሳብ ባይኖረኝ ምን ማድረግ አለብኝ?**

መ. ወርሃዊ ኪራይ መክፈያ 30ኛው ቀን ላይ በቂ ሂሳብ ባይኖርዎ በቀጣይ 7ቀናት ውስጥ መክፈል እንዲችሉ የእፎይታ ጊዜ ውስጥ ይገባሉ፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ኪራዩን ከከፈሉ መደበኛ አገልግሎቱን ከእነ ግል ማህደርዎ እንደነበረው መቀጠል ይችላሉ፤ ነገር ግን በዚህ የእፎይታ ጊዜ ውስጥ ክፍያውን ባይፈጽሙ የተለመደውን የደወል ድምጽ ወደሚያዳምጡበት የእግድ ጊዜ (15 ቀን) ይሸጋገራሉ፡፡ በነዚህ ጊዜያት (15 ቀናት) ክፍያውን ሳይፈጽሙ ቢቀሩ ሙሉ በሙሉ ከአገልግሎቱ ይሰረዛሉ፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ጊዜ ውስጥ ኪራዩን ከከፈሉ መደበኛ አገልግሎቱን ከእነ ግል ማህደርዎ እንደነበረው መቀጠል ይችላሉ፤

**ጥ. አገልግሎቱን በምን በምን ቋንቋዎች መጠቀም እችላለሁ?**

መ. አገልግሎቱን በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች መጠቀም ይችላሉ

**ጥ. ወደ 822 የሚላኩ አጭር የጽሑፍ መልዕክት የምጠቀምበትን ቋንቋ እንዴት መለወጥ እችላለሁ?**

መ. የሚጠቀሙበትን ቋንቋ አማርኛ ለማድረግ ወደ 822 በአጭር የጽሑፍ መልዕክት L1 ብለው ይላኩ እንግሊዝኛ ለመጠቀም ደግሞ ወደ 822 L2 ብለው ይላኩ፤

ጥ. ስለ አገልግሎቱ ተጨማሪ መረጃ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

መ. ስለ አገልግሎቱ ተጨማሪ መረጃ እና ድጋፍ ለማግኘት በአጭር የጽሁፍ መልዕክት ወደ 822 H ብለው በመላክ መረጃ ማግኘት ይችላሉ ወይም የሲ.አር.ቢ.ቲን ድረ ገጽ www.crbt.et ይጎብኙ፡፡

Q. የአገልገሎት ደንበኝነቴን እንዴት ማቋረጥ እችላለሁ?

መ. ወደ 822 በአጭር የጽሑፍ መልዕክት U ብለው በመላክ የአገልገሎት ደንበኝነትዎን ሙሉ በሙሉ ማቋረጥ ይችላሉ፡፡

<u>ለተጨማሪ መረጃ ወደ ነጻ የጥሪ ማዕከላችን 994 ይደውሉ ወይም የሲ.አር.ቢ.ቲን አገልግሎት ድረ ገጽ www.crbt.et ይጎብኙ፡፡</u>